<u>የዜና አንባቢዎችን የየበከለ ችግሮች</u>

<u>በሰይፉ ኣዳነች ብሻው</u>

የየበከለ የሚለውን ቃል የ"የበከለ" ብዬ መጻፍ ነበረብኝ። ግን ድፍን አድርጌ የጻፍኩት ለምክንያት ነው። ምክንያቱም አንድ ጽሑፍ በትክክል ካልተጻፈ በስህተት ሊነበብ እንደሚችል፣ ትክክል ካልሆነ ደግሞ ግራ ሊያጋባ እንደሚችል ለማሳየት በማለት። የየበከለን ሲያነቡት የህትመት ስህተት ሊመስል ስለሚችል የሚነበቡ ቃላት ደግሞ በትክክል ካልተነበቡ ጣዕማቸውን ያጣሉ። **የበከለ** የሚለው ቃል ደግሞ መጥፎ ቃል ሊመስል ይችል ይሆናል። በዚህ ጽሑፍ ግን የበከለ "**የ**" "**በ**" "**ከ**" "**ለ**" የሚሉት ተገጣጠሙ የቀረቡ ናቸው። የወሰድኳቸውም "<u>**የ**</u>ማን" "<u>**በ**</u>ማን" "<u>**ከ**</u>ማን" "<u>**ለ**</u>ማን" ከሚሉት ቃላት ላይ ነው። "ማን" የሚለውን ቃል "የት" ወይንም "ምን" በሚለው ቃል ተለውጦ ሊገባም ይችላሉ።

አማርኛ ሲጻፍ በነጥቦች(:) ማለትም በነጠላ(፣) በድርብ(፤) ተለይቶ በአራት ነጥብ(።) በጥያቄ(?) በአንክሮ(!) በሥላቅ(¡) ሊዘጋ ይችላል። በነገራችን ላይ የሥላቋን ምልክት(¡) አቤ ቶኪቻው እንዴት እንደማይጠቀምባት አልገባኝም፤ ስለሆነም ራሱኑ ፈልጌ እጠይቀዋለሁ።

አማርኛ በእጅ ሲጻፍም ሆነ በዘመናዊ ህትመት እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ቃላቱ በነጥብ ይለዩ ነበር። ከዚህ በታች ያለው በ1944 ዓ.ም. አቆጣጠራችን ራስ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው "አርሙኝ" በሚል ርዕስ ካሳተሙት የአጫጭር ልቦለዶች መድብል ውስጥ "አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም" ከሚለው ድርሰታቸው ውስጥ እንደ ምሳሌ የተወሰደ ነው። ይኸም ኹለት ነገሮችን ለመገንዘብ ያስችለናል። አንደኛ፡- በአንድ ድምፅ/ትንፋሽ የሚወጡና አንድ ትርጉም ያላቸው ቃላት በነጥብ መለየታቸውን ለማሳየት ሲኾን (ጥንት በሕትመት ሥራዎች ኹሉ ሳይቀር የነጥብ ግልጋሎት ነበር) ኹለተኛው ደግሞ በነጥብ ወይንም በባዶ መሥመር ካልተለየ ከ"ኣ" "ፐ" እና "ና" በስተቀር በግሉ ተለይቶ የሚነበብ ሞኄ እንደሌለ ለመግለፅ ነው። የነዚኸም አገልጋሎት "ኣ" ለማቃሰት ወይንም ጉዳት ሲደርስ የሚወጣ የድንጋጤ ወይንም የሲቃ፤ "ፐ" ነገርን ለማቅለል ወይንም ለንቀት፤ እና "ና" ደግሞ "ቀረብ በል" ወይንም "እና" የሚለውን መስተፃምር አሳጥረው ሲጽፉት ወይንም ሲናገሩት የሚገኝ ነው። እዚች ላይ "አ"ን ጨምሩልኝ ቃለአጋኖአዊውን።

"የ" "በ" "ከ" "ለ" ከቃላት በፊት በመግባት "ማን" "የት" ወይንም "ምን" በሚሉ ጥያቄዎች የቃላቱን አቅጣጫ ወይንም ትርጉም ወግ የሚያሲዙ ናቸው። ሲነበቡ አብረዋቸው ካሉት ቃላት

ጋር በአንድነት እንጂ ተነጥለው ድምፅ በማውጣት ትንፋሽ ከዋጡ በኋላ ወደ ቀጣዩ ቃል የሚያስኬዱ አይደሉም።


፫፻፲፮ አልሞትኹም ፡ ብዬ ፡ አልዋሽም ። 316

እቶ ፡ ተማቹ ፤ ወይ ፡ ግሩም ፡ ሞት ፡ ላይቀር ፡ በገዛ ፡ ቤቱ እስረኛ ፡ ሆኖ ፡ የሚገድለውን ፡ ጠላት ፡ ከመጠበቅ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ተነሥቶ ፡ በጠላቱ ፡ ላይ ፡ አይወድቅበትምን ፤ ድር ፡ ቢያብር ፡ አንበሳ ፡ ያስር ፡ ይበላል ።

እንደ ፡ ርቢ ፡ በጎች ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ለጠላት ፡ ከመመቸት፡ ይልቅ ፡ የክብር ፡ ሞት ፡ መሞት ፡ አይሻልም ፡ ነበር ።

ከላይ የተሠመሩትን ቃላት ልብ ይበሉ። የ፣ በ፣ ከ ወይንም ለ የሚሉት ጥኄያት ክብር፣ መጠበቅ፣ መመቸት እና ጠላት ከሚሉት ቃላት ጋር ተገጣጥመው እንጂ (የ ክብር፣ በ ገዛ፣ ከ መጠበቅ/ከ መመቸት ወይንም ለ ጠላት) ተብለው ተለያይተው ስላልተጻፉ እንደ የቀድሞው አስተታተም የ: ክብር፣ በ: ገዛ፣ ከ: መጠበቅ/ከ: መመቸት: ወይንም: ለ: ጠላት: ተብሎ: የተጻፈ: ባለመኾኑ: በአንድ: ላይ: ማለትም: አንድ: ቃል: መኾናቸውን: ለማሳየት: በአንድ: ትንፋሽ: መነበብ: ያለባቸው: ናቸው። የነጥብ ዋና ሥራው አንድ የሆኑ ቃላትን አሰባስቦ ከሌሎች ጋር እንዳይደባለቁ በማድረግ ትርጉም ባለው መንገድ እንዲነበቡ የሚያደርግ ነው። የቃሉን አባባል ዘዬ ያስይዝልናል ማለት ነው። በዘመኑ መሣሪያ ሲጻፍ ግን ነጥቡ ባዶ ሥፍራ እየተሰጠው እንዲለይ ሆኗል።

እያደር የማዳምጣቸው ዜናዎች ፈሊጥ የያዙ ይመስለኛል በየ… በ… ከ… እና ለ… ጥኄያት የሚጀምሩት ቃላት ላይ ማላዘን በብዛት አጋጥመውኛል። በኢትዮጵያ… ከማለት ይልቅ በ*(ማላዘን)*ኢትዮጵያ…፣ ከአሜሪካ… የሚለውን ከ*(ማላዘን)*አሜሪካ…፣ ለእሥረኞች… ብሎ በአንድነት ከማንበብ ይልቅ ለ*(ማላዘን)*እሥረኖች… የአካባቢው… የሚለውን የ*(ማላዘን)*አካባቢው… ብሎ ማንበብ ዓይነት ማለት ነው። ግን ትክክል አይደለም። እርግጥ በግል ሃሳብን ለመግለጥ አንድ ግለሰብ የጠፋበትን ሃሳብ ለማሰባሰብም ኾነ የቱን ብል ይሻለኛል በሚል ምክንያት ለጊዜ መግዣ ቢያላዝን፤ ጣሪያ ጣሪያ ቢመለከት፤ ጉሮሮውን ቢያጠራ ከሃሳብ ፍሰት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ብዙም አያስጨንቅም። ግን ዜና ሲነበብ… ሥራው ማንበብ መሆን ይጠበቅበታል እንጂ ምን ልበል በማለት ጥኄያትን አንቆ መሸጋገሪያ መፈለግ የዜናው ገፅ ካልጠፋና መስመር ካልሳቱ በስተቀር (ይኽም የሚደጋገም መሆን አይኖርበትም) ለአድማጭ ጆሮ ጥራት የጎደለው ኾኖ ማቅረቡ ትክክል አይመስለኝም። ዜና ሲቀርብ ጆሮን እንዲጥመው ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ከበቅርብ ጊዜ ጀምሮ ጆሮዬ ከገቡት ቃላት መካከል... ይቅርታ *ከቅርብ* ጊዜ ጀምሮ ብዬ አባባሌን ላርመው... "ከባለፈው" የሚል ቃል በተደጋጋሚ ለመስማት አጋጥሞኛል። እዚህጋ የበከለን መልሼ ላምጣ። ከባለፈው በየመቼ? (በ)መቼ? ከመቼ? ለመቼ? ምን መባል እንዳለበት እንመልከት። የመቼ? ሲል *ያለፈው*፤ (በ)መቼ? ሲል ደግሞ *ባለፈው*፤ ከመቼ? ለሚለው ደግሞ *ካለፈው*፤ እንደዚሁም ደግሞ ለመቼ? የሚለው ደግሞ *ላለፈው* ይላል እንጂ የያለፈው፣ በባለፈው፣ ከባለፈው፣ ለላለፈው አይልም። በነገራችን ላይ ይኸንን የመሰለ ስህተት በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አለ። ልብ ካሉት ያገኙታል።